# አርዮሳውያን

ከመሠረት ስብሐት ለአብ።

በመካነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጀ።

አዲስ አበባ 1985 ዓ.ም.

# አጭር መግለጫ።

ይህን ጽሑፍ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ከሚል አርዮሳውያን እንዲታረሙበት ከተጻፈው መጽሐፍ፥ ሃያ አራተኛውን ተራ ቍጥር የያዘ ክፍል ሲሆን፣

እርሱም «አርዮሳውያን ትልቅና ትንሽ አምላክ አለ» በማለት አምልኮ ባዕድን ለመፍጠር ስለመንግማታቸው» በሚል ርዕሰ ነገር የቀረበው ነው።

በዚህ ርዕስ ያለው ፍሬ ነገር አርዮሳውያን ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ የሚኖር እግዚአብሔር አምላክ፥ አምልኮተ ባዕድን የማይፈቅድና ፈጽሞም የሚቃወም መሆኑን ባለመገንዘባቸው፥ ትንሽ አምላክን ፈጥሮ፥ በእርሱ ዓለማትን ፈጠረ ብለው የሚናገሩ ሲሆን፥ በዚያ ትይዩ ደግሞ ይህን የአርዮሳውያንን አባባል የሚቃወም በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የተብራራ ትምህርታዊ መልስ ተሰጥቶበት ይገኛል።

በነገራችን ላይ፥ እውን እግዚአብሔር ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አርዮሳውያን እንደሚናገሩት አድርጎ ይሆን? የለም አላደረገም፡ በእውነቱ እግዚአብሔር አምላክ አርዮሳውያን እንደሚሉት አላደረገም ፈጽሞም አያደርግም ስንኳን እርሱ ራሱ ብዙ አማልክትን ለሚሠሩና ለሚያመልኩ ትንሽ ፍጡር አምላክን በመፍጠር አብነት ሊሆን ቀርቶ፥ ሰዎች ከአሳባቸው ፈጥረው፥ ከልባቸው አንቅተው ልዩ ልዩ አማልክትን ሲሠሩ ቢያያቸው እንኳ፥ በጣም ይቆጣል። ይፈርድባቸዋልም። ዘጸአ. 20፥ 2-6። ራእ. 21፥8።

ታዲያ ጉዳዩ እንዲህ ሆኖ ሳለ፥ ብዙ አማልክትን እየሠሩ ለሚያመልኩ ሰዎች እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሥራ መሪያቸው ሆኖ፥ የመጀመሪያ ንድፍ /ሞዴል/ እንዲሆንላቸው ብሎ አንድ ትንሽ ፍጡር አምላክን በመፍጠር የአማልክትን አሠራር እንዳሳየ አድርጎ መናገር፥ አባባሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ትይዩ የቆመ ተቃራኒ ነገር አይደለምን?

መችም አርዮሳውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ በመሆን የቆሙበት ዓላማ ውጥን፥ አማልክትን በማብዛት ፍላጎታቸውን ለማርካት አስበው ይሆናል።

ይሁን እንጂ ልዑል እግዚአብሔርን ያህል አምላክ፡- ጣዖታትን ያመልኩ ዘንድ አማልክትን ለሚሠሩ ሁሉ፥ የሥራ መሪ በማስመሰልና፥ ትንሽ አምላክን ፈጥሮ የሚያሳይ የጣዖትን አሠራር ጀማሪ በማድረግ አቅርበውት ይገኛሉና፥ ይህ ድፍረታቸው በዓመፅ ላይ ዓመፅ እየጨመሩ ሄደው ወደባሰው ሁኔታ ለመውደቅ እንዳበቃቸው፥ ከማንም የሚሠወር አይሆንም።

እንግዲህ አምልኮ ባዕድን ይፈጥሩ ዘንድ የተነሣሡ አርዮሳውያንና ሌሎች መሰሎቻቸው ከወደቁበት ከአምልኮተ ባዕድ ማጥ እንዲነሡ፥ እውነተኛ አምላክና የእውነተኛ አምላክ አምልኮ አቋም እንደምን ባለው መሠረት ላይ ጸንቶ እንደሚኖር ጠንቅቀው ያውቁ ዘንድ ይገባቸው የለምን? እነሆም የመጽሐፍ ቅዱስን ኃይለ ቃል፡- በበቃ አኳኋን እንዲረዱና እንዲያስተውሉ ታስቦ፥ በዚህች ጽሑፍ በመጠኑ ተብራርቶላቸዋል።

ይህም «ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ እውነትንም ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነው» ሲል ሐዋርያው በተናገረው መሠረት ነው። 1 ጢሞ. 2፥3-4።

ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ፥ እውነትንም ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ እውነትም አርነት ታወጣቸው ዘንድ የእኛም ደስታ ነውና፥ ከዋናው መጽሐፍ ቀጥሎ በወጣው በዚህ ጽሑፍ እንዲጠቀሙበት እንመኝላቸዋለን።

መሠረት ስብሐት ለአብ።



# አርዮሳውያን «ትልቅና ትንሽ አምላክ አለ» በማለት አምልኮ ባዕድን ለመፍጠር ስለመነሣሣታቸው።

አርዮሳውያን ፍጡርን ለማምለክ ስለፈለጉ፥ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ፍጡር አድርገው ለማሳየት በልዩ ልዩ መንገድ እንደተጣጣሩ ካለፉት ምዕራፎች ስንመለከት መቆየታችን ይታወሳል። ይህንም እውነትን እየሸፈኑ እውነት ያልሆነውን ግን እውነት ለማስመሰል፥የሚጥሩት ጥረት ባላቸው አሳብና ጉልበት ሁሉ በመሆኑ፥ በትዝብት እንድንመለከታቸውና እንድናተኩርባቸው አስገድዶናል።

ከዚህም አንዱ ቀጥሎ ያለው ነው።

እርሱም፡- የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ፍጡር እንደሆነ አስመስለው ለማሳየት ከመሞከራቸውም በላይ፥ ትንሽ አምላክ አድርገው ለማምለክ፥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሥን ጽሑፍ ባህላዊ አሠራር የምዕመናንን ዓይን በሚያጥበረብር ሁኔታ እያብረዘረዙ ለመጠቀም ጥረት ማድረጋቸው ነው።

አርዮሳውያን በእግዚአብሔር ቃል ወልድ ላይ ምንም እንኳ ጉዳት ሊያደርሱበት ባይችሉም፥ በተቻላቸው መጠን በሌላና ይህን በመሳሰለ ነገር ፍጡር አምላክ ወይም ትንሽ አምላክ አድርገው ለማሳየት መሞከራቸው ስለምንድን ነው? ይህን ያህልስ መጣጣራቸው ለምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ፥ ፍላጎታቸው አምልኮ ባዕድ ሆኖ ይህንኑ በመጽሐፍ ቅዱስ አስታከው ለመመሥረት ከጅለው እንደሆነ ለመገንዘብ እንችላለን።

ይኸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባህላዊ የሥን ጽሑፍ አሠራር የምእመናንን ዓይን ልቡና ለማጥበርበር ከሞከሩባቸው ክፍሎች አንዱ ወንጌላዊ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ በምዕራፍ 1ቍ. 1/ቃል እግዚአብሔር ነበረ/ ብሎ የጻፈውን ነው።

እነሆም አርዮሳውያን ይህን ጌታ የሚወደውና ታማኝ ደቀመዝሙሩ የሆነ ዮሐንስ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ሲል የጻፈውን በማሳበል ሌላ ዓይነት ተቃራኒ ትርጉም ፈጥረውለታል።

ይህም ሲያሳብቡና ሲያብሉ የፈጠሩት ፈሊጥ በዚሁ ጥቅስ ዮሐንስ «እግዚአብሔር» ያለውን ለውጠው የእውነተኛ እግዚአብሔር ወይም የትልቅ አምላክ ስም ሳይሆን፥ «የፍጡር አምላክ ወይም የትንሽ እግዚአብሔር ስም ነው» የሚል ነው።

ታዲያ ትንሽ እግዚአብሔር ወይም ፍጡር አምላክ በዚሁ ዮሐንስ በጻፈው ጥቅስ ውስጥ ምን ሊያደርግ መጣ? ከየትስ መጣ? የሚል ጥያቄ ሲቀርብባቸው፥ ቀጥሎ ያለውን መልስ ይሰጣሉ

አትስገድላቸውም አታምልካቸውም።... እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» ዘፀአ. 20፥2-6። ዘዳግ. 5፥6-10።

ይህ ትእዛዝ ከዓሠርቱ ቃላት የመጀመሪያው ነው። ታዲያ አርዮሳውያን «ከእኔ በቀር» የሚለውን ኃይለ ቃል ሊያስቡበት ይገባ አልነበረምን? ካሰቡበትስ እንደገና ትንሽ አምላክ አለ እያሉ አንድነው ይጨምሩበታልን? ወይስ ብቻውን ሆኖ እንዳይጎዳ አገቡውለት ይሆን?

«አንባቢ ሆይ፥ መቼም ይህን ሁሉ አይተሃል። እንዲሁም ቀጥለን የዚህ ተመሳሳይ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እናቀርባለንና በጥንቃቄ ተመልከታቸው፡- «ከእኔ በቀር፥ ወይም ከእርሱ /ከእግዚአብሔር/ በቀር በሚሉ፥ እንዲሁም «ሌላ የለም» በሚሉ ቃላት እግርጌ አሥምርባቸውና፥ እስቲ እነዚህን ቃላት በአንዱ ሕያው አምላክ ጎን ወይም አንጻር ትንሽ የሚባልን አምላክ አሹልከው ያስገቡ እንደሆን በትኩረት እያቸው።

«አንተስ ብትሰማኝ ሌላ አምላክ አይሆንልህም። ለሌላ አምላክም አትሰግድም። ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና።» መዝ. 80/81/፥ 9፡10።

«ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤ ከእኔ በኋላም አይሆንም። እኔ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም። ተናግሬአለሁ አድኜማለሁ አሳይቼማለሁ በእናንተ ዘንድ፥ ባዕድ አምላክ አልነበረም፥ ስለዚህ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር።» ኢሳ. 43፥10-13።

«ከማኅፀን የሠራህ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሁሉን የፈጠርሁ፤ ሰማያቱን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ለብቻዬ ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም።» ኢሳ. 44፥24።

«እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ከእኔ ሌላ ማንም የለም፥ ከእኔም በቀር አምላክ የለም።» ኢሳ.45፥5፡ 6-18።

«ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱም ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም መኖሪያም ልትሆን እንጂ፥ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላል። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለም። በስዉር ወይም በጨለማ ምድር ሥፍራ አልተናገርሁም።»... ኢሳ.45፥18-20።

«ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? እኔ ጻድቅ አምለክና መድኃኒት ነኝ። ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም። እናንተ የምድር ደርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና ከእኔ በቀር ሌላ የለምና፥ ወደ እኔ ዞሮር በሉ ትድኑማላችሁ።» ኢሳ. 45፥21፤23።

«አቤቱ የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ በሰማይ ወይም በምድር አንተን የሚመስል አምላክ የለም።» 2ዜና መዋዕ. 6፥14።



«ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ እነዚህ አማልክት ከምድር ላይ ወይም ከሰማይ በታች ይጠፋሉ ትሉአቸዋላችሁ።» ኤር. 10፥11።

«ከአንዱም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» እኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን።» 1ቆሮ. 8፥4፡ 6።

«አንዳንዶች እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ» 1ቆሮ. 10፥7።

«ስለዚህ ወዳጆቼ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ» 1ቆሮ.10፥14። «ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለም ድረስ... ክብር ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን። አሜን» ይሁዳ 1፥28።

አስተዋይ አንባቢ ሆይ፥ ይህን ሁሉ በብሉያትም በሐዲሳትም የተጻፈውን አይተሃል። እስቲ መልካም ፈቃድህ ይሁንና ደግሜ በመናገሬ ሳትሰለቸኝ፥ ከነዚህ ከተመለከትኻቸው ጥቅሶች ሁሉ « ከእኔ በቀር ሌላ የለም» «እኔ ብቻ ወይም እርሱ ብቻ አምላክ» በሚሉና ልዑል እግዚአብሔር ስለ ራሱ ማንነት እየገለጸ በተናገራቸው እግርጌ አሥምርባቸውና ኃይለ ቃላቶቹን በትኩረት ተመልከታቸው።

ታዲያ የእነዚህ ያየሃቸው ቃላት ነበልባላዊ ነጸብራቅ ሕያው በሆነ በአንዱ አምላክ ፊት ወይም አጠገብ ትንሽ የሚባል አምላክ ለማስቀረብና ለማስጠጋት፥ እጉኑም ለማስቆም የሚያስችሉ ሆነው ይታዩህ እንደሆን እስቲ በእውነቱ ፍረድ ኢሳ.44፥6፡ 7።

እንግዲህ አርዮሳውያን ስለገናናነቱ ታላቅ ተብሎ በሚጠራው በእግዚአብሔር ንጽጽር፥ ትንሽ አምላክ እንዳለ አድርገው የሚናገሩት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መሠረት የሌለው እንደሆነ ልታስተውል ትችላለህ።

«መኑ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር ወመኑ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ፡- ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማነው? ከአምላካችንስ በቀር እግዚአብሔር ማነው?» መዝ.17/18/፥31።

ከዚህ በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ ሲነገር እንደተመለከትነው ሁሉ፥ በልቡናው አስቦ ሰማያትንና ምድርን ያሉባቸውንም በቃሉ የፈጠረ በአፉ እስትንፋስም ያጸናቸው እግዚአብሔር፥ ቅድምና ተድኅሮ /ቅደም ተከተል/ ታናሽ ታላቅ፥ ባህላዊውና በባሕርዩ ህልውና እንደሌለበት ገልጾአል። መዝ.32/33/፥6። እንዲያውም እንደዚህ ካለው ስሕተት መጠበቅ እንደሚገባ እያስጠነቀቀ አስገንዝቦአል።

አርዮሳውያን ግን በኋላ የተፈጠረ ትንሽ አምላክ እንዳለ ይናገራሉ? ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ «አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኃራዊ አልቦ ባዕድ አምላክ እምቅድሜየ ወእምድኅሬየ። እኔ መጀመሪያ ነኝ፥ እኔ መጨረሻ ነኝ ከእኔ በፊት አምላክ የለም ከእኔ በኋላም አምላክ የለም» ሲል የተናገረው

በዚህም ይዞታ:- በአምልኮተ ባዕድ የሚገኙ ፍጡራን ከእግዚአብሔር ውጭ ተጥለው እንዲወድቁ የሚያደርጋቸውን ነገር ስንመረምር፥ ከሁለት መንሥኤዎች ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚሁ ነገር መንሥኤዎቹ ሁለቱ መሠረታውያን ሁኔታዎች ናቸው ማለት ነው።

እነርሱም:-1ኛ. ለባውያን ፍጡራን ከገዛ ራሳቸው አፍልቀው የሚያመጡት ጠንቅ ሲሆን፥

2ኛ. ለባውያን ፍጡራን ከሕሊናቸው አፍልቀው በሚያመጡት ጠንቅ ላይ፥ ከእግዚአብሔር ከማይለወጥ እውነታዊ ባሕርዩ የተነሣ፥ ሲከታተላቸው የሚታየው ፍርድ ነው። ሮሜ 1፥18። 2፥15፤16።

መጀመሪያ ነገር:- ለባውያን «ፍጡራን የገዛ ራሳቸው ከሚያመጡት መዘዝ የተነሣ ነው» ስላልነው ከዚህ ቀጥለን እንናገራለን።

1ኛ. አዎን፥ ለባውያን ፍጡራን የእግዚአብሔር አምላክነት የባሕርዩ መሆኑን እያወቁ፥ ወደዚሁ የባሕርዩና የግሉ ወደሆነው የአምላክነቱ አምልኮት፥ ባዕድ የሆኑ ፍጡራን ሊጨመሩበት ደፍረው ሲጠጉት፥ እሳተ መለኮቱ ወጥቶ ያቃጥላቸዋል ይኸውም ወደ ባሕርዩ አምላክነት በርኩስ ልባቸው ደፍረው በሚያቀርቡት ላይ ስለሚቀደስ ነው። ዘሌዋ. 10፥1-3።

2ኛ. ለባውያን ፍጡራን የእግዚአብሔርን የባሕርይ አምላክነቱን ዐውቀው፥ ለዚሁ ለባሕርይ አምላክነቱ የሚገባ ክብር ምስጋና አምልኮትና ስግደት እንዲያቀርቡለት ታስበው ነው የተፈጠሩት። በዚሁ ፋንታ ግን ይህ ለእርሱ እንዲያቀርቡለት ተፈልገው የተፈጠሩበትን መሠረታዊ አቋም ዘንግተው፥ ከእርሱ ወስደው እንደዲያብሎስ ለራሳቸው ሲመኙት፥ ወይም ለሚወዱት ለሌላ ፍጡር ሲሰጡበት፥ ከገዛ ራሳቸው የሚያመጡት የውድቀት መዘዝ ነው። ዮሐ. 8፥44። ሮሜ 19፥23።

ከእግዚአብሔር ከማይለወጥ እውነታዊ ባሕርዩ የተነሣ ለባውያን ሆነው ተፈጥረው ሳለ፥ እውነትን በሚረግጡ ፍጡራን ላይ የሚመጣው መቅሠፍትና ቅጣት እንደምንድን ነው? ቢሉ:-

ሐዋርያው ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን እውነት በዓመፅ ለሚቃወሙ የእግዚአብሔር ቊጣ፥ ከሰማይ ይገለጣል» ባለው መሠረት ሲፈጸም የሚታይ ነው። ሮሜ 1፥18።

1ኛ. እንደሚታወቀው ሁሉ እግዚአብሔር ራሱ የእውነት አምላክ ነው። በባሕርዩም ውሸትን የማይወድ እውነተኛ አምላክ ነው፥ እውነትንም ይጠብቃታል፤ የባሕርዩ ናትና:- መዝ. 145/146/፥6። ም. 118፥137።

በዚሁ አንጻር ደግሞ፥ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚገባውን የራሱን የባሕርይ ገንዘቡ የሆነውን አምልኮትና ስግደት ክብር ምስጋና፥



ፍጡር የራሱ ገንዘብ ያደርገው ዘንድ ቢሰርቅበት፥ ወይም በውሸት ወስዶ ለሌላ ፍጡር ሲሰጥበት ቢገኝ፥ እውነትን እንጂ ውሸትን በማይወድ ባሕርዩ ይቀጣዋል ይቆጣዋልም። 2 ነገ. 17፥15-20።

ምክንያቱም ልዑል እግዚአብሔር በባሕርይ ዳኝነቱ «ፈታሒ በጽድቅ፥ ኰናኒ በርትዕ» ማለት በእውነት የሚፈርድ በቅንነት ሚዳኝ የውሸት ጠላት ነውና ራእ. 19፥11።ዮሐ. 8፥44።

2. ለልዑል እግዚአብሔር ያለው አምልኮት፥ ክብር ምስጋና ስግደት፥ የባሕርዩ ነው እንጂ፥ ተውሶ ተበድር ያመጣው አይደለም። የባሕርዩ ገንዘብ ለሌላ ሊሰጡበት ፈልገው፥ ከእርሱ ዘንድ ሊፍቁበት ሲፈልጉ፥ እሳተ መለኮቱ ከራሱ ወጥቶ ያቃጥላቸዋል። ዕብ. 12፥29። ዘዳግ. 4፥24።

3. ለባውያን ሆነው የተፈጠሩ ፍጡራን እግዚአብሔር የሚመለክበት የሚሰገድለት ክብር ምስጋና የሚሰጠው ማን ሆኖ ቢገኝ እንደሆነ፥ ፍጡራን ግን እነማን እንደሆኑ፥ ለይተው የሚያውቁበት የሕሊና ዕውቀት አላቸው። ይህን የመለየት ሥልጣን ካወቁና ዕውቀቱ ካላቸው፥ አመዛዝነው ለማን እንደሰጡት ዐውቀዋል ማለት ነውና፥ ላልተገባው ቢሰጡ ይቀጣቸዋል። ይህም የጽድቁና የርትዑ መንገድ ነው።

እንግዲህ ይህን በደኅና አእምሮ ከተረዳ በኋላ፥ የልዑል እግዚአብሔርን እውነት፥ በሐሰት ለውጠው «እንደ አምላክ እንሆናለን» ብለው በተነሡ በሰይጣንና በመልአክተኞቹ፥ በአዳምና በሚስቱ እግዚአብሔር የፈረደው ፍርድ ቅጣት «ያለ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ነው» የሚል አመዛዛኝ ሰው ይኖር አይመስለንም። ኢዮብ 34፥10-15።

2ኛ. ሌላው ጥያቄ ደግሞ አሁንም ይኖራል። ጥያቄውም:- እግዚአብሔርን እንደዚያ የደፈረው ዲያብሎስ እንደ አምላክ ልሁን ብሎ በተቃራኒነት ቢነሣበት ነው፥ እነዚያ ከእርሱ ጋር የወደቁት መላእክት ግን፥ እንደ ዲያብሎስ «አማልክት እንሁን» ብለው አልተነሡበትም። ታዲያ ለምን አልራራላቸውም? ለምንስ እስከዚህ ድረስ ጨከነባቸው? የሚል ነው። 2ጴጥ. 2፥4።

መልሱ:-

በርግጥ ነው- እነዚያ የወደቁት መላእክት ዲያብሎስን እንደ አምላክ አድርገው አዩትና ተገዙለት እንጂ፤ የገዛ ራሳቸው «እንደ አምላክ እንሁን በልዑል እንመሰል» አላሉም ራእ. 12፥4፡9።

ነገር ግን የአምልኮተ ባዕድ መሠረታዊ ይዘቱ ምንድን ነው? ለአምላካዊ ባሕርዩ የሚገባውን ነጥቆ፥ ለፍጡር መስጠትና ፍጡርን እንደ አምላክ አድርጎ፥

ራስን አስሞሽቶ በሐሰት ለፍጡር ስግደት አምልኮት ምስጋናም /ስብሐት/ ማቅረብ አይደለምን?

ስለዚህ ከዲያብሎስ ጋር የወደቁት መላእክት የገዛ ራሳቸው እንደ አምላክ ለመሆን ባይመኙም፥ ዲያብሎስ መልአክ ሆኖ እንደ እነርሱ የተፈጠረ፥ ፍጡር ገዙር መሆኑን እያወቁ ሳለ፥ «እንደ አምላክ ነኝ» በሚልበት ጊዜ፥ ውሸትን መርጠው ሕሊናቸውን በመርገጥ፥ ለባሕርይ አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር የሚገባውን አምልኮትና ስግደት ክብርና ምስጋና ሰጥተውታልና፥ ሊፈርድባቸው የተገባ ሆነ። ይሁዳ ቁ.6። ስለዚህ ነው ያለ ርኅራኄ ሲፈረድባቸው የሚታየው።

መቼም አምልኮተ ባዕድ ልብን የሚመለከት ነው። ማንም ቢሆን የልዑል እግዚአብሔርን ቦታ ለፍጡር ሰጥቶ ሲገኝ፥ ሌላ አምላክ ማምለኩ መሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአል። ይህ የአእምሮ መሸነፍና ውድቀት ነውና። 2ጴጥ. 2፥19። እነሆም ጠቢባን መላእክት በአእምሮአቸው አልተሸነፉም። በአምልኮተ ባዕድ እንዳይወድቁም ይጠነቀቃሉ። ራእ. 19፥10። 22፥8፡9።

ልብ ለልዑል እግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ የሆነውን ክብርን፥ ምስጋናን ችሎትን ጽንዕን፥ ሥልጣንን ኃይልን ማዳንንም መንግሥትን ክሂሎትን በምልዐት መገኘትን፥ ፍጹምነትን ከልዑል እግዚአብሔር ውጭ እንደሚገኝና የትም ዘንድ ሊኖር እንደሚችል ካሰበ፥ አስተሳሰቡ በአምልኮተ ባዕድ የተያዘ መሆኑ ግልጽ ነው። ኤር. 17፥5-8።

3ኛ. በዚህ ጊዜ ደግሞ ታዲያ በአምልኮቱ የተነሡበት ያለ ትዕግሥትና ያለ ርኅራኄ ፈጥኖ የሚጥላቸውና የሚቀጣቸው ከሆነ፥ በከፍተኛ ባለሟልነት ላቀረባቸውም ያለትዕግሥት ያለ ርኅራኄ የሚቀጣቸውና የሚፈርድባቸው ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥትና ርኅራኄ ፍቅርም ከምን ላይ ነው? እያለ የሚጠይቅ ሰው ይኖራል።

1. መጀመሪያ ነገር ልዑል እግዚአብሔር እውነተኛና ጻድቅ ቅዱስ ስለመሆኑ የተነጋገርንበት መሆኑን እናስታውሳለን።
2. ልዑል እግዚአብሔር ወደ ራሱ አቀረበውና ባለሟልም አድርጎታል እንጂ ያ ፍጡር በሙያው ወይም በሥራው ጀብዱ በባለውለታነቱ ባለሟልና ቀራቢ ለመሆን የበቃ፥ የገዛ ራሱን ያቀረበ አይደለም እኮ። ዮሐ. 15። በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ይህ ነው።

አዎን፥ ልዑል እግዚአብሔር ማንም ሳያማክረው፥ ማንም ሳይረዳው ማንም ሳያበድረውና ሳያውሰው ሁሉን ነገር ከገዛ ራሱ እንደሠራ፥ ሁሉ ለእርሱ፥ ሁሉ በእርሱ፥ ሁሉ ከእርሱ እንዳደረገ የታወቀ ነገር ነውና። ሮሜ 11፥33-36።

እንግዲህ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ፥ ልዑል እግዚአብሔር የማንንም ውለታ አልበላም። ያ ባለሟልነት ያገኘው ፍጡር እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መጠን ሊያመልከውና ሊሰግድለት ሊያከብረው ይገባዋል እንጂ፥ ሊንቀውና



ሊያቃልለው ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ሊወስድና ለገዛ ራሱ ወይም ለወደደው ፍጡር ሊሰጥበት ይገባዋልን?

መቼም ቢሆን በትክክለኛ ልቡና የሚያስብ ከሆነ፥ በእውነተኛው አምላክ ላይ ይህን የመሰለ የቅጥፈት ሥራ አይሠራበትም። አምልኮተ ባዕድ የስሕተት ኃጢአት ብቻ አይደለም። የንቀትና የድፍረትም ውጤት ነው። ዘዳግ. 32፥21። ኤር. 44፥15-17። ሆሴ. 6፥7።

ፍጡሩ እንደዚህ ሆኖ በሚያገኘው ጊዜ ነው እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ሆኖ በጽድቁና በርትዑ ሊፈርድበት የሚገደደው። ለራሱ ክብር ፈጥሮት ሳለ፥ የተገላቢጦሽ ሲንቀውና ሲያቃልለው እያየው! የዱር ባለሟሉ፥ ወዳጄ ነበረ ብሎ ሊታገሠው አይችልም። ይህ በጽድቁና በርትዑ የሚፈርደው ፍርድ ነውና። ናሆም 12፥8። ዘዳግ. 32፥10-17።

እንግዲህ ጠያቂው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የእግዚአብሔር ቅዱስ ጠባይ እንዴት እንደሆነ የተማረ ሰው ከሆነ፥ ይህ ከላይ የተገለጸውን በገዛ ራሱ መርምሮ ሊያመዛዝን ይቻለዋልና፥ ጥፋቱ ከፍጡራን እንደሆነ፥ ወይስ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ያስተውላልና፥ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን ጨካኝ ብሎ ሊወቅሰው ይችላል።

አርዮሳውያን ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የተገባውን ጥያቄ በመጠየቅና ለጥያቄው መልስ ሆኖ የቀረበውን ገለጻ ሊያጠኑት አይፈልጉም። በዚሁ ፋንታ ሌላ መንገድ ሲፈጥሩና፥ በዚያው ብቻ ሲመሩ እናያለን።

አርዮሳውያን የፈጠሩትን አዲስ መንገድ እንደሚከተለው እናቀርበዋለን።

ይኸውም፡-

አርዮሳውያን /እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን/ ብለው በሰየሙት መጽሐፋቸው የእግዚአብሔር ቃልን «ከእግዚአብሔር ፍጥረቶች አንዱ እርሱን ዲያብሎስ ያደረገው... የዚህ ዓለም አምላክ የሚባለው ከመፈጠሩ ከብዙ ጊዜ በፊት ተፈጥሮ ነበር።» ማለታቸው ይታወሳል። /እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን/ ገጽ 38፥ መሥመር 16-19። ተመልከት።

አርዮሳውያን እውነተኛና የባሕርይ አምላክ የሆነውን እግዚአብሔር ቃል ወልድን ከባሕርያዊ የአምላክነቱ ግርግ አውርደው «ፍጡርና ትንሽ አምላክ ነው» ማለታቸው፥ የተቀባ ኪሩብ ከመሆኑ ወጥቶ፥ በትዕቢቱና በውሸቱ ከወደቀው ከዲያብሎስ ጋር፥ በማጋራትና በማጉዳኘት የእኩያነትንና የአቻነትን ደረጃ ሰጥተው ለማስተካከል መጣጣራቸው፤ እንደተለመደው ለስድብ ያመቻል ብለው እንጂ፥ እውነትስ ሌላ ጠቃሚ ነገር ኖሮአቸው አይደለም። ዓላማቸው የእግዚአብሔርን ልጅ መስደብና ዲያብሎስንም ከፍ አድርገው ከፍርድ ነፃ ለማድረግ መሆኑ፥ ማናቸውም ሰው ቀጥሎ ባለው ሐተታ ጠልቆ ቢመረምር ወዲያው ይረዳዋል።

1. የአርዮሳውያን አስተሳሰብ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ፍጡር ይሉና ፍጡርና ትንሽ አምላክ የሚባል ከሆነም፥ ዲያብሎስስ ፍጡር አይደለም ወይ? እንዲባልላቸው።

2. ለእግዚአብሔር ቃል ወልድ የሚቀርበው ስግደት ምስጋና ፍጡርና ትንሽ አምላክ በመሆን ደረጃ የሚቀርብለት ከሆነስ፥ ዲያብሎስም ለራሱ እንዲሰገድለትና ምስጋና እንዲቀርብለት ቢመኝ፥ ጥፋተኛ የሚያደርገው ምንድን ነው? እንዲባልላቸው ነው። ይሁን እንጂ፥ የእግዚአብሔር ቃል፥ ወልድ ፍጡር ሳይሆን እውነተኛ አምላክ መሆኑ፥ ዲያብሎስ ግን የሐሰት አባት ተብሎ የወደቀበት ምክንያት ራሱ ፍጡር መሆኑን እያወቀ ሳለ፥ የማይገባውን ስግደትና አምልኮት ለራሱ ከመመኘቱ የተነሣ መሆኑ፥ አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተገለጸ፥ ዓላማቸው ውድቅ ሆኖአል። ዮሐ. 8፥44። ሕዝ. 28፥15-19።

አርዮሳውያን በቅንነት ቢያስቡበት ኖሮ፥ ይህን ሁሉ እንደ ሚያስከትልባቸው አጥተውት አይመስልም። ነገር ግን እውነተኛና የባሕርይ አምላክ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ከባሕርይ አምላክነቱ አውርደው፥ ፍጡርና ትንሽ አምላክ ለማድረግና፥ ፍጡር ግቡር የሆነውን ዲያብሎስን ደግሞ፥ ከእግዚአብሔር ቃል ወልድ ጋር አስተካክለው በፍጡርነት ደረጃ አቻውና እኩያው እንደሆነ አስመስለው ለማሳየት ፈልገው ነው። እንዲያውም ከሰይጣን ይልቅ፥ ዝቅ ያለ አእምሮ እንዳለው አድርገው ለማሳየት ሲፈልጉ፥ ወልደ እግዚአብሔር «የዲያብሎስን መንገድ ተከትሎ ከዲያብሎስ ጋር አላሴረም» ሲሉ በንግግር ብቻ ሳይሆን በጽሑፍ አስፍረውት እናያለን። /እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን/ በሚል መጽሐፋቸው ገጽ 39 መሥመር 16፡17። ተመልከት መቼም እንደዚህ ያለ የድፍረት ቃል ከሰዎች አንደበት ሲሰማ ለጆሮ የሚዘገንን ነው።

3. ይህን ብቻ አይደለም ፍጡርና ግቡር የሆነ ዲያብሎስ ከመልአካዊ ደረጃው የወደቀበት «በልዑል እመስላለሁ፤ እንደ አምላክ እሆናለሁ» ብሎ በመመኘቱ የሠራው ኃጢአት፥ የዓመፃ ኃጢአት እንዳይደለ ለማሳየትም ይሞክራሉ።

ሌላ ቀርቶ በኋለኛው የፍርድ ቀን እንኳ «ዲያብሎስ በአንድ ጊዜ ይረሸንና ተቃጥሎ አመድ ይሆናል እንጂ፥ ለዘላለም እየተቃጠለ ወደሚኖርበት ገሃነመ እሳት አይጣልም» እያሉ በገሃነመ እሳት ላይ ውኃ ስብከታቸውን ይረጫሉ፥ ለነገሩ ደጋግ ጠበቆች ሆነው ቆመውለታል «እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን» ገጽ 58።

የዚህን ያህል የሚጥሩት ምን እንዲያገኙ ነው? ብለን በመገረም እንጠይቅ ይሆናል። መቼም መጽሐፍ ቅዱስ ሲሡሩት የዋሉትን



እያፈረሰባቸው ነው እንጂ፥ እነርሱማ በሚከተሉት ዝርዝር ነገሮች ግባቸውን ለመምታት ነው ጉምጅተው የነበረ።

ሀ. ወልድን «ፍጡርና ትንሽ አምላክ ነው» በማለተ ሌሎች ትንንሾች አማልክትም በብዛት ሊኖሩ እንደሚቻል አስመስሎ ለማሳየት፥

ለ. «የዚህ ዓለም አምላክ እያሉ በግጋነን ለሚያደንቁለት ለዲያብሎስ የአምላክነት ቦታ እንዲገኝለት ለማመቻቸት፥

ሐ. ዘለዓለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ግን፥ ከብዙ የጣዖታት አማልክት ጋር ተርታ አሰይዘው፥ በአምልኮት ወረፋ ተፋላሚ አድርገው ለማሳየት ነበረ አሳባቸው።

ታዲያ አንዱን የእግዚአብሔር ልጅ ለማዋረድ ሲሉ ይህን ሁሉ ቢያከታትሉ፥ ሰይጣን ርእሰ ዓመፃ የሆነበትን የአምልኮ ባዕድ ፍልስፍናውን /ኃጢአቱን/ «ወንጀል» እንዳልሆነ ለማሳየት የቆሙለት ጥብቅና ይይዝላቸው ይሆን? የለም፥ ይህ ዓላማቸው በፍጹም የማይሆን ነገር ነው።

ሰይጣን ርእሰ ዓመፃ የሆነውን ባዕድ አምልኮን መፍጠሩ፥ /መፈልሰፉ/ ቀላል ወንጀል ለማድረግ ለማንም አይቻለውም። አሁንም የባዕድ አምልኮን ወንጀል ቀላል አድርጎ የሚገምት ሰው ቢኖር፥ ሰይጣን ሲፈጠር ተሰጥቶት ከነበረው ከኪሩባዊ መዓርግ የወደቀው ስለምን ነበረ? ብሎ ይጠይቅ፥

ሰይጣን የወደቀው የገዛ ራሱ ፍጡር ግቡር መሆኑን ረስቶ፥ እንደ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ሊሰገድለትና ሊመለክ ስለፈለገ አይደለምን? ዮሐ. 8፥44። ኢሳ. 14፥12-15። ማቴ. 4፥9-10።

ያለዚያማ ሲያመነዝር ተገኝቶአል ይባላል? ወይስ የሚበላና የሚጠጣ ሆኖ ሆዱን ሊያጠግብ ሲሰርቅ ተይዞአል ይባላል? ብሎ እንዲያስብ እናመለክተዋለን።

ይህን ከዚህ በላይ የታተተውን ሐተታ ካየን ዘንድ፥ የአርዮሳውያን ፍላጎት ምን እንደሆነ ሳንረዳ አንቀርም።

## የአርዮሳውያን ፍላጎትና ዓላማ በተነገረው አሳብ ውስጥ እንደምን ሆኖ ነው የሚታየን?

በዚህ ክፍል ውስጥ አርዮሳውያን ከተከተሉት መንገድ ሲያንጸባርቅ ያገኘነው እንደሚከተለው ሆኖ በዝርዝር ቀርቦአል።

1ኛ. የአንዱን እውነተኛ አምላክ አምልኮትና ስግደት ምስጋና ትልቅና ትንሽ፥ የትንሽ ትንሽ እያሉ፥ አማልክት የሚያበዙበትን የትውልድ ዘርፍ መሥርተው ለአንዱ አምላክ የሚገባውን አምልኮቱን ለየፍጡራት በታትነውና አሰራጭተው ብክንክን ለማድረግ ሆኖ እናገኘዋለን።

እንደ እውነተኛ አምላክ ተደርጎ እንዲታይ ታስቦ በጥራዝ ነጠቅ ስልት የሚጠቅሰውን የሙላ ጥቅስ አይቀበሉትም። አስተሳሰቡ ከመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ውጭ ነውና። ማቴ.4፥6።

ሰይጣን የዓለም ገዥ ወይም የዓለም አምላክ የተባለበት ምክንያት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ መሠረት እንደሚከተለው ሆኖ ይገለጻል።

መጀመሪያ ነገር በክርስቲያኖች ዘንድ ሰይጣን ዲያብሎስ ተጥሚና በተወዳዳሪነቱ የጸና አምላክ እንደሆነ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። «የዓለም አምላክ ወይም የዓለም ገዥ» የተባለበት ምክንያት ግን ቀጥሎ እንዳለው ነው።

1ኛ. ዲያብሎስ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ማለት ለሰው ልጆች ሁሉ አባትና እናት የሆኑትን አዳምንና ሔዋንን በሐሰት ሸንግሎ በማታለል፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እንዲኮበልሉ አደረጋቸው፥ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር አምላክ እንዲፈርድባቸው ሆነ።

2ኛ. አዳምና ሔዋን ለባውያን ሆነው ተፈጥረው ሳለ፥ ለዚሁ ለሰይጣን አእምሮአቸውን አሳልፈው እስኪሰጡ ድረስና፥ ራሳቸውን በማታለሉ ሥር እስኪጥሉ ድረስ ወደቁለት። ስለዚህም ያታለላቸው ሰይጣን አእምሮአቸውን ለመግዛት ዕድል አገኘ። ዘፍጥ. 3፥1-19።

3ኛ. የአዳምና የሔዋን ልጆችም በእግዚአብሔር ዓለም በእግዚአብሔር ጥበቃና መጋቢነት እየኖሩ ሳለ፥ ከወላጆቻቸው በወረሱት ውዱቅ ጠባይ የተነሣ፥ ሰይጣን እንደ ላመ ልጆች፥ እንደ አውራው ውላጆች አድርጎ ስለተጠቀመባቸው፥ ሰይጣንን ማምለካቸው የተረጋገጠ ነው።

እነሆም ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ዓለም እየኖሩ ሳለ፥ ሰዎች ለሰይጣን ስለተገዙለትና ስላመለኩት፥ «ሰይጣን የዓለም ገዥ፥ የዓለም አምላክ» ተብሎአል። ከዚህ በስተቀር ግን ሰይጣን ዓለምንና በእርስዋ ያለውን እንደፈጠረ፥ ወይም ከእግዚአብሔር በኃይል ቀምቶ እንደ ወሰደበት እየታሰበ «የዓለም አምላክ» አይባልም ሮሜ 5፥12-11።

ዓለምና በእርስዋ ያለ ሁሉ የእግዚአብሔር አምላክ ነው። ይህን ሁሉ የፈጠረ የሚመግብ የሚያስተዳድር ያው አንዱ ኃያል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። መዝ. 23/24/፥1፡2። የሐዋ. 17፥24-27።

በእግዚአብሔር ዓለምና ሕይወት እየኖሩ ሳለ፥ እግዚአብሔርን ረስተው ሰይጣንን በሚያመልኩት ዘንድ ዲያብሎስ የዓለም አምላክ ቢባል፥ እርሱ በእውነት አምላክ ሆኖ አይደለም። አይሆንምም።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ምሳሌን ብንወስድ፥ በዓለም እየኖሩ ሰይጣንን እንደአምላክ አድርገው በማያዩትና በማያመልኩት ሰዎች ዘንድ፥ ሰይጣን አምላክ እንዳልሆነና፥ አምላክም እንደማይባል ግልጽ ነውና።



ታዲያ አንዳንዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥራዝ ነጠቅነት ስልት ተጠቅመው «የዓለም አምላክ ነው» እያሉ ቢሰብኩለት፥ ይህ አባባላቸው ሰይጣንን እርግጠኛ አምላክ ለመሆን ያበቃዋል ወይ? መዝ. 23/24/፥1-3። የሐዋ. 17፥24።

ደግሞ እነዚህ አሁንም ዲያብሎስን «የዓለም አምላክና ገዥ ነው» የሚሉ ሰዎች ባያውቁ ነው እንጂ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተሸርባቸዋል። ዲያብሎስ ለሰው ልጆች ሁሉ ወላጆች የሆኑትን አዳምንና ሔዋንን አታልሎ፥ የልጆቻቸውን አእምሮ አጨልሞና አኑሳቁሎ፥ በራሱ መንገድ እየመራ ሲጠቀምበት የነበረ የጨለማና የኍራኞንት አገዛዝ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በዕርገቱም እንደተገፈፈና እንደተነጠቀ ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተገር የታወቀ አይደለምን? ቆላ. 2፥13-15። 1፥13፤14።

የዓለም መንግሥትስ ለአምላካችንና ለበጉ እንደሆነች በመጽሐፍ ቅዱስ ተረጋግጦ የለምን? ራእ. 12፥10፤11። 11፥15። 5፥12።

ከዚህ የተነሣም ዲያብሎስ ሰውን ተቆራኝቶ ሲገዛበት የነበረ የጨለማ ሥልጣኑም ስለተገፈፈ፥ ሰዎች ከጨለማ ወደ ብርሃን፥ ከሰይጣን ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ዓይናቸውን የሚከፍት ወንጌል ታውጆ ሲሰበክ መገኘቱ በጣም ግልጽ አይደለምን? የሐዋ. 26፥17፡18።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኮ በሞቱና በትንሣኤው በዕርገቱም ሰይጣንን ሽር ወደ ውጭ እንዲጣል ሲያደርግ መጣሪያውን ከእጁ ነጥቆታል። ማቴ. 12፥29። ኢሳ. 49፥25። 53፥12።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ሁሉ በፍቅሩ ቤዛ ሆኖ፥ ለመስቀል ሞት በሚዘጋጅበት ጊዜ፥ «አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል። አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል። እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊዜ፥ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ» ሲል ተናገር እንደነበረ ይታወሳል። ዮሐ. 12፥21፡32።

እነሆም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ «የዚህ ዓለም ፍርድ አሁን ደርሶአል የዚህ ዓለም ገዥም አሁን ወደ ውጭ ይጣላል» ብሎ የተናገረው፥ ቃል ወዲያው ነው ፍጻሜውን ያገኘ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ፥ በሰይጣን ላይ የተፈጸመው ድል አድራጊነት እንደምን ባለ አኳኋን እንደተከናወነ ሐዋርያው ጳውሎስ ያሳየናል።

«በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንን በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወገደው። አለቆችንና ሥልጣናትንም ገፍፎ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጽ አሳያቸው» ይላል። ቆላ. 2፥14፡15

ዳግም ወደ ዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ልጆች በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው! በሕይወታቸውም ዘመን ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ነፃ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» እያለ የምስራች ቃሉን አሰምቶአል። ዕብ. 2፥14፡15።

ሰማይና ምድር በእግዚአብሔር ቃል ተፈጥረዋል እንጂ፤ በፍጡራን አልተፈጠሩምና ነው። ኤር. 10፥11፤12። ዕብ. 11፥3።

ኢየሱስ ወደ ምድረ በዳ ሊፈተን በሄደ ጊዜ፥ አርባ ቀንና ሌሊት ከጾመ በኋላ፥ ከዲያብሎስ የቀረበለት ፈተና አንዱ ይህ አምልኮ ባዕድ ነበር።

ዲያብሎስ መቼም ከትዕቢታዊ ውድቀት የተነሣ ደፋርና ይሉኝታ ቢስ ሆናአልና፥ ምድርና ሞላዋ፥ ዓለምና በእርስዋ የሚኖሩ ሁሉ ለእግዚአብሔር መሆናቸውን ዘንግቶ፥ በውሸቱ ምንም ሳያፍርበት፥ «ለእኔ ወድቀህ ብትሰግድልኝ የዓለም መንግሥታትንና ክብራቸውን ሁሉ፥ እሰጥሃለሁ» በማለት ኢየሱስን መፈታተኑ የሚዘነጋ አይደለም። ማቴ. 4፥8። መዝ. 23/24/፥1-2።

ኢየሱስ ግን «አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ» ተብሎ ተጽፎአል።» ሲል እንዳሰፈረው እናውቃለን። ማቴ. 4፥8-9። ሉቃ. 4፥5-8።

እነሆም ስለ አምልኮ ባዕድ ተቃውሞ በእግዚአብሔር አብና በልጁ የተገለጸው የማስጠንቀቂያ ትምህርት የቱን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ለመገንዘብ ይህ ብቻ በበቃ ነበር።

ኢየሱስ «ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና፥ ብሎ የተናገረው ቃል፥ ለዲያብሎስ ከትርጉሙ ሳይገባው አልቀረም። የዚሁ ትርጓሜ፡-

«እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ በመሆኑ መጠን ሊያመልኩት ሊሰግዱለት ክብር ምስጋናም ሊሰጡት ይገባል። ምክንያቱም በእውነት አምላክ ነውና።

አምልኮ ስግደት እውነተኛ ለሆነ አምላክ ብቻ ይሰጣል እንጂ፥ እንደገበያ ዕቃ ይህን እሰጥሃለሁና ስገድልኝ» እየተባለ፥ በውለታ አይሸጥም። ባጭሩ እንደዚህ ያለው ክቡር ነገር እውነተኛ ላልሆነ አምላክ አይሰጥም። አምልኮት በጥቅምና በስለት በፍርሃትም አይለወጥምና። ዳን. 3፥16-18።

«አንተ ሰይጣን ግን ስገድልኝ በማለትህ እውነተኛ አይደለህም። ውሸተኛ ነህ። ስለዚህ ስንኳን ሊሰገድልህ ለወንጀለኛ የሚገባ ቅጣት ተፈርዶብህ ትቀጣለህ» የማለት ኃይለ ቃል መሆኑን ለሰይጣን ተሰምቶታል። ስለዚህ ሸሽቶ ሄዶአል።

ኢየሱስ «አምልኮትና ስግደት ለእውነተኛው አምላክ እንጂ፥ ለሌላ እንደማይሆን ለሰይጣን ያስረዳው ነገር ለአርዮሳውያን ገብቶአቸው ይሆን? ካልገባቸው፥ መቼም ከሰይጣን ይልቅ ብሰዋል ማለት ነው። ከለማበት የተጋባበት ይባላልና።

እግዚአብሔር እርሱን ብቻ እንዲያመልኩት ለባውያን አድርጎ የፈጠራቸው ሰዎች ከእርሱ ማለት ከባሕርዩ መለኮቱ ባዕድና ፍጡር የሆነውን «አምላክ» ብለው እንዲያመልኩ እንዲሰግዱለት አይፈቅድምና አይፈልግም።



ይኸውም፡- ክብሩንና ምስጋናውን ለሌላ እንዲሰጡበት ስለማይፈቅድና ስለማይፈልግ ነው።

እነሆም የነዛ ራሱ በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ ቀጥሎ ያለውን የማያከራክር ኃይለ ቃል ተናገር እንደዘጋው እናያለን።

«ኢይሁብ ክብርየ ልባዕድ መስብሐትየ ለግልፎ።

«ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬን ለጣዖት አልሰጥም» ብሎአል።

ኢሳ. 42፥8።

አዎን፥ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነውና፥ ሊያመልኩትና ሊሰግዱለት ክብር፥ ምስጋናም ሊሰጡት ይገባል። የባሕርይ ገንዘቡ ነውና፡- ከእግዚአብሔራዊነት ባሕርይ ውጭ ለሆነ ፍጥረት ግን ማምለክ፥ እንዲሁም ስግደት፥ ክብር ምስጋና መስጠት በነቢያትና በሐዋርያት በጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተከለከለ መሆኑን በሚከተሉትም ጥቅሶች ለመመልከት ይቻላል።

«ፀሐይ ጨረቃን ከዋክብትንና የሰማይን ሠራዊት ሁሉ ባየህ ጊዜ፥ ሰግደህላቸው አምልከሃቸው እንዳትስት ተጠንቀቅ» ዘዳግ.4፥19።

«አንተስ ብትሰማኝ ሌላ አምላክ አይሆንልህም፥ ለሌላ አምላክም አትሰግድም፥ ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና» መዝ. 80/81/፥8-10።

«እስራኤል ሆይ ስማኝ ልመስክርብህ፡- እምላክህስ እኔ አምላክ ነኝ» መዝ. 49/50/፥7።

«የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸውና፤ እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ። ምስጋና ውበት በፊቱ፥ ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸውና» መዝ. 95/96/፥5-6።

አንባቢ ሆይ፥ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ስለ አምልኮት ከተነገሩት መካከል «ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ብቻ ስገድ፤ እርሱን ብቻ አምልክ» ተብሎ መነገሩን «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ሌሎች አማልክት በፊቴ አይሁኑልህ አትስገድላቸው አታምልካቸው። እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» ተብሎ መጻፉን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተረድተሃል። ልዑል እግዚአብሔር ይህን ብቻ ሳይሆን፥ እንዲህ ያለበትንም ምክንያት ሲገልጽ «ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለጣዖት አልሰጥም» ብሎ ድርሱን ገልጾ እንዳስታወቀ ተገንዝበሃል። እንግዲህ አምልኮት ስግደት ክብር ምስጋና /ስብሐት/ የአንዱ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቦች በመሆናቸው ለፍጥረት የማይሰጣቸው መሆኑን ከዚህ ላይ ባለው ኃይለ ቃል እንደማያዳግም ሆኖ ተገልጾአል። ኢሳ. 42፥8።

ይህም፡-

እግዚአብሔር ለማናቸውም ነገር ወይም ፍጡር ክክብሩና ከስብሐቱ /ምስጋናው/ እንደማይሰጥና፥ ለፍጡራንም ሊሰጠው እንደማይፈቅድ አረጋግጦአል። ይህን የሚያሳየን ፍጡራን በፍጡርነታቸው አቋም ከመለኮታዊ ባሕርዩ የማይዛመዱ ስለሆኑ፥ ፍጡራን ግቡራን በሆኑበት አቋም ለዘለዓለማዊ ባሕርዩ ምን ጊዜም ባዕድ ናቸውና ነው።

ስለዚህ ይህን አምልኮትና ክብር ስግደትና ምስጋና ሊሰጥ ያልፈቀደበት ምክንያት ከርትዕና ከእውነት ከቅንነትና ከትክክለኛነት ባሕርያዊ ፍትሑ የተነሣ ሆኖ ይገኛል።

የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉ ይህን በመገንዘባቸው በትምህርታቸው ሆነ በምሳሌነታቸው ተጠንቅቀው ሲጠብቁት እናያለን።

እናንተ ግን ወዳጆቼ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ። ይሁዳ 17-25።

ሐዋርያት ጳውሎስ በርናባስም ሊያመልኩአቸው መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው ለመጡ ሰዎች እናንተ ሰዎች ለምን እንደዚህ ታደርጋላችሁ? እኛ ደግሞ እንደ እናንተ ሰዎች ነን። ከዚሁም ከከንቱ ነገር ተመልሳችሁ ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን» እንዳሉዋቸው እናገኛለን። ዮሐ. 14፥14-16።

ጳውሎስም «ከአንዱም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» 1ቆር. 8፥4። «አንደንዶች እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ። ስለዚህ ወዳጆቼ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ» ብሎአል። 1ቆር. 10፥6፡14። የሐዋ. 15፥29።

ዮሐንስም «ልጆቼ ሆይ ከጣዖት ራሳችሁን ጠብቁ» ብሎአል። 1ዮሐ. 5፥21። ራእ.2፥14። 21፥28።

አርዮሳውያን ግን ይህን ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረውን እያዩ፥ ከገዛ ሐሳባቸው ፈጥረው ከእውነተኛው ከባሕርይ አምላክ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ውጭ «ትንሽ አምላክ አለ። ፍጡር አምላክ አለ» እያሉ፥ የባዕድ አምላክ አምልኮትን ወደ እውነተኛው አምላክ ወደ እግዚአብሔር መለኮታዊ መንግሥት ሊያስጠጉ ይፈልጋሉ።

እግዚአብሔር ግን፥ ከባሕርየ መለኮቱ ውጭ የሆነ ባዕድ ፍጡር ነገር ፈጥሮ፥ ወደ ባሕርያዊ አምልኮቱና ክብሩ እንደማያስጠጋ ከላይ እየተመለከትናቸው ከመጣን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በግልጽ ተመልክተናል።

በእውነቱ፥ አርዮሳውያን ሰዎች ይህን የአምልኮት ነገር፥ የመዳንም የመጥፋትም መሠረት ነውና፥ ለጥፋት እንዳልተፈጠሩ የሚያምኑ ከሆኑ፥ ጠለቅ ብለው በጥንቃቄ ቢያስቡበት መልካም ነበረ። ኢሳ. 28፥16።



እግዚአብሔር ክብሬንና ምስጋናዬን ለሌላና ለባዕድ አልሰጥም ብሎአልና አርዮሳውያንስ ክብሩንና ምስጋናውን የገዛ ራሳቸው ለፈጠሩት ፍጡር በመስጠት ባያባክኑበት፥ እስከዚህ ድረስ ምን ይቸግራቸው ነበር?

እንዲያውም በእልክ፥ የእግዚአብሔርን ባሕርያዊ መብት ለመንጠቅና ከእጁ አውጥቶ ለባዕድ ሰጥቶ ባዕድ አምልኮትን ለመመሥረት የዚህን ያህል መታገል የሚገርም ነው። ያውም፡- ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ያዋጣናል ብለው ይሆን?

1. አርዮሳውያን እግዚአብሔር የገዛ ራሱ ፍጥረታትን በመፍጠሩና በመጠበቁ እየተመካበት ሳለ፥ የሠራውን የገዛ ሥራውን ለፍጡር ሲሰጡበት ዮሐ. 1፥3።
2. እግዚአብሔር «አምልኮቱንና ክብሩን ምስጋናውን ለፍጡር አልሰጥም» እያለ ሳለ፥ በገዛ ሥልጣናቸው አዳይና አደላዳይ ሆነው ለፍጡር ሲሰጡበት የሐዋ. 17፥24፡29።
3. እግዚአብሔር ማዳኑን በራሱ እጅ አድርጎ በማዳኑ የገዛ ራሱ ሊመሰገንበት እያስታወቀ ሳለ፥ የአድኅኖን ተግባር ሁሉ ለፍጥረት ሲሰጡበትና የገዛ ራሱን ግን ውልቁን ሊያስቀሩት ሲዘጋጁ መገኘታቸው፥ በሚታዘባቸው ዘንድ አስተሳሰባቸው ያሳዝናል እንጂ፥ እርሱስ አምላካዊ መብቱን አሳልፎ ለማንም አይሰጥም። ኤር. 44፥28-29። የሐዋ. 4፥12። ራእ. 20፥15።

## የእግዚአብሔር ቃል ወልድ እውነተኛ አምላክ ነው።

በዚህ ርእስ ነገር የምናየው ጥሬ ንባብ ሐዋርያው ዮሐንስ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ገልጾ ያስታወቀበት ኃይለ ቃል ነው።

ጥቅሱም እንደዚህ ይላል፡-

«የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን። እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን። እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው። ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ።»

1ዮሐ. 5፥20፡21።

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ለሚያውቅና ለሚያምን ሰው እውነተኛውን ነገር አረጋግጠ ለመያዙ፥ ማንም ሊያስተባብለው በማይችል በዚህ ቃል ተመስክሮለታል።

ይህ ብቻ አይደለም የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን «እውነተኛ አምላክ የዘለዓለም ሕይወት» መሆኑን በግወቁና በግሙት ደግሞ ማየታትን ከማምለክ ይጠበቅበታል። ምክንያቱም እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዞአልና ነው።

የጌታው ታማኝ መልእክተኛ የሆነው ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ባለው ግልጽ ትምህርት ነው! ወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን የመሰከረለት ዮሐ. 1፥1-4። 2ዮሐ. 1፥9።

አንባቢ ሆይ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ህልው የሆነ አብም በእርሱ ህልው የሆነ፣ ከእውነተኛ አምላክ ከእግዚአብሔር የመጣ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ተገንዘብ። ሐዋርያው ዮሐንስ «እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው» ሲለው አስተውለህ ተገንዝበሃልን? 1ዮሐ. 5፥19-21።

እስቲ «የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው» በሚል እግርጌ አሥምርበትና ቀጥለን ካስቀመጥናቸው ጥቅሶች ጋር አመዛዝነህ የትምህርቱን መሠረት መርምር፡- ዮሐ. 1፥1፡18። 14፥9-11። 7፥29። 8፥42። 10፥28-30። ሮሜ 9፥5። 1፥3፤4። ዕብ. 1፥1-3።

የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ አምላክ በመሆኑም ከእግዚአብሔራዊነትና መለኮታዊት ህልውና ባዕዳን ለሆኑ ለፍጡራን ማየታት የማይሰጥ ክብር፣ ምስጋና ስግደት ሲሰጠው ታያለህ። ፊልጵ. 2፥6-11።

ታዲያ ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ እያለ በሚያስተምርበት ጊዜ፣ አርዮሳውያን ወልድን ወይም ቃልን «ትንሽ አምላክ ወይም ፍጡር አምላክ» የሚል አብነት ከየት ነው ያገኙት? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ወልድን ፍጡር አምላክ ወይም ቃልን ትንሽ አምላክ ሲያደርገው አይገኝም።

ይኸውና መጽሐፍ ቅዱስ ወልድን «እውነተኛ አምላክ ነው» ሲለው የሚገኝ። ወልድን «የእግዚአብሔር ቃል ነው» ሲለው የሚገኝ የወልድ ክብርም ለአባቱ አንድ የሆነ ልጅ ባለው ክብር መጠን መሆኑን ነው የሚገልጸው።

ባጭሩም ወልድ በአንድ እግዚአብሔራዊት ህልውና ያለና የሚኖር መሆኑን፣ የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ፣ የአካሉም ምሳሌ ከእርሱ ዘንድ ያለ፣ የነበረ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወጣ፣ በሥጋም የመጣና የተገለጸ የመለኮቱም ምልዐት በሰውነቱ የታወቀበት መሆኑን ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስታውቅለት፡- ዮሐ. 1፥3። 14፡18። ዕብ. 1፥1-3። 1ጢሞ. 3፥16። ዮሐ. 14፥9። ቈላ. 2፥9።

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ሥጋ በሆነና ከድንግል ማርያም ተወልዶ በሥጋ በተገለጸ ጊዜም፣ በባሕርያዊ ምልዐተ መለኮቱ እንዳለ ነውና፣ በእግዚአብሔርነቱ ሲሰገድለት እናያለን።

ለምሳሌ፡-



1. በኮከብ ተመርተው፡- ወደ ተወለደው ሕፃን የመጡ ሰብአ ሰገል ወድቀው ሰገዱለት። ማቴ. 2፥11።
2. ደቀ መዛሙርትም በታንኳ ውስጥ ሆነው ሰገዱለት። ማቴ. 14፥33።
3. ከሙታን እንደተነሣም አሥራ አንዱ ሐዋርያት ወድቀው ሰገዱለት። ማቴ. 28፥16።
4. ይከተሉት ከነበሩት ሴቶች ማርያም መግደላዊትና ሁለተኛይቱ ማርያም ወድቀው ሰገዱለት። ማቴ. 28፥9።
5. ሌሎችም የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ጊዜ እንደሰገዱለት የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት ይቻላል። ዮሐ. 11፥32።

እነርሱም ዕውር ሆኖ የተወለደውና ኢየሱስ ዓይኑን ያበራለት፣ ለምጻሙ ሰው፣ የመቶ አለቃውና ሌሎች ናቸው። ዮሐ. 9፥38። ማቴ. 8፥2። ማቴ. 9፥18። ሉቃ. 17፥15-18።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ለምን ሰገዱለት? ብለን እንጠይቃለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የወጣ ወልደ እግዚአብሔር፣ በሥጋም የተገለጸ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ቢረዱና ቢያውቁ አይደለምን? ዮሐ. 16፥26-30። ሮሜ 1፥4። 1ጢሞ. 3፥16።

አርዮሳውያን ግን እነዚህ ሁሉ ነ. ..ሉለት ትንሽ አምላክ በመሆኑና ተአምራቱን አይተው ስለፈሩና የሚይዙትን ስላጡ ነው ይሉ ይሆናል! ይላሉም።

ይሁን እንጂ፣ ይህ የአርዮሳውያን አባባል ልክና እውነት አይደለም። መጀመሪያ ነገር ብቻውን አምላክ የሚሆን ልዑል እግዚአብሔር፣ ሰዎች እንዲያመልኩትና እንዲሰግዱለት ብሎ ትንሽ አምላክ ፈጥሮና ሠርቶ ማየት አላቆመም። ይህም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በሰፊው ማስረጃ ስንሰጥበት መቆየታችን የሚዘነጋ አይደለም።

ሁለተኛ ነገር «ለእግዚአብሔር ልጅ የሰገዱለት ሰዎች ተአምራቱን ባዩ ጊዜ፣ ደንግጠው ወይም ፈርተው ነው» ሲሉ አርዮሳውያን ከአሳባቸው ያወረዙት የእብለት ትችት ከእውነት ውጭ የተሠነዘረ ነው። ይህንም ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በጥንቃቄ ማየት ነው።

ለኢየሱስ የሰገዱለት ሰዎች ማንነቱን ስላወቁና በትክክለኛ አእምሮ በጭምትነት ስላስተዋሉት ነው።

1. ከሰገዱለት ሰዎች መካከል አንዱ ዕውር ሆኖ ተወልዶ ሲኖር፣ ኢየሱስ የፈወሰው ነው። የሐዋ. 9፥1-7። በዕውርነት ተወልዶ የነበረው ሰው ፈሪሳውያን እንዴት እንደዳነ በሚመረምሩት ጊዜ፣ ኢየሱስ እንዳዳነውና ስለ ኢየሱስ ሲናገር «ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር» ብሎ ለፈሪሳውያን በቂ ማስረጃ ሰጥቶአቸዋል። ዮሐ. 9፥32-33።

እነሆ ዕውሩ የተናገረው ቃል ኢየሱስ ራሱ «የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑብኝ» ሲል ለአይሁድ እንደተናገራቸው ያለ ነው። ዮሐ. 10፥37።

ይህም ኢየሱስ ማን እንደሆነ ተመርምሮ ከሚታወቅባቸው የምርምር መርሆዎች አንዱ ነው።

ኢየሱስ ባገኘው ጊዜም በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? ሲለው፥ እርሱም መልሶ በእርሱ አምን ዘንድ ማነው? ሲል በጥንቃቄ ከጠየቀ በኋላ፥ ኢየሱስ «አይተኸዋል፥ ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው» አለው። በዚህም ጊዜ ከዕውርነት የዳነው ሰው «ጌታ ሆይ አምናለሁ ብሎ ሰገደለት»። ዮሐ. 9፥35-38።

እነሆም ይህ ሰው ለኢየሱስ ሲሰግድለት ማን እንደሆነ ዐውቆ ጠይቆ አረጋግጦ እንጂ፥ በድንጋጤ እንዳልሆነ ልናስተውል እንችላለን። ዮሐ. 24፥33።

2ኛ. ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሰገዱለት ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጴጥሮስ አንዱ እንደሆነ እናውቃለን። ይህም ጴጥሮስ ሊሰገድለትና ሊመለክ የማይገባውን፥ ከሚገባው ለይቶ የሚያውቅ ሰው እንደሆነ እናውቃለን። ራሱ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት በሄደ ጊዜ፥ ቆርኔሌዎስ ሰገደለት። ጴጥሮስ ግን የቆርኔሌዎስን ስግደት ዝም ብሎ ሊቀበለውና ሁኔታውን ተመልክቶ በትዕግሥት ሊያልፈው አልተቻለውም። ነገር ግን፥ የቆርኔሌዎስን እጅ ይዞ «ተነሣ! እኔ እንደ አንተ ሰው ነኝና» ብሎ ቆርኔሌዎስን አስነሣው። በዚህም ለፍጡር ሰው መስገድ እንደማይገባ ገልጾ አስተማረው። የሐዋ. 10፥25-26።

እነሆም፡- ጴጥሮስ ስለ ስግደትና አምልኮ ከማይገባ ቦታ ሲውል በሚያይበት ጊዜ፥ ለእግዚአብሔር አምላክነት የዚህን ያህል ቀናተኛና የባዕድ አምልኮትን ተቃዋሚ ሲሆን፥ ለጌታው ለኢየሱስ ክርስቶስ ግን፥ እርሱ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ስላወቀውና ስላመነበት፥ ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት አንዱ ሆኖ በግንባሩ ወድቆ ሲሰግድለት እናያለን። ማቴ. 28፥17።

ታዲያ ይህን አስተውሎ ያየና የተመለከተ ሰው፥ «ጴጥሮስን ደንግጦ ልቡን አጥቶ ወይም ፈርቶ ነው ለኢየሱስ የሰገደለት» ብሎ ቢያስተባብል፥ እንደዚህ ዓይነት ሰው በእውነት ጸንቶ እንደቆመ ሰው ይቈጠራልን? በመጽሐፍ ቅዱስ ተመርሆ ልቡናዊስ እውነተኛ በያኝ ለመሆን ይበቃልን?

ዳግም፡- ራሱ ኢየሱስ በአምልኮ ባዕድ ለተፈታተነው ሰይጣን «ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ፥ እርሱን ብቻ አምልክ ተብሎአል» ሲል በገዛ ራሱ ከነተግሣጹ ጋር እንደተናገረው እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ ከዚህ በላይ እንዳየን፥ ለእርሱ ሲሰግዱለት ለተገኙት ስግደታቸውን ተቀበለላቸው እንጂ፥ አልከለከላቸውም።

አርዮሳውያን በእውነት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል የሚመረምሩ ከሆኑ፥ ቀጥለው ባሉት አሳቦች ላይ እስቲ ፍርድ ይስጡ፡-



ኢየሱስ በአምልኮ ባዕድ ለተፈታተነው ሰይጣን «ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ፥ እርሱን ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል» ብሎ ለምን ገሠጸው? ሰዎች እየወደቁ ለእርሱ በሰገዱለት ጊዜ ደግሞ ስግደታቸውን ለምን ተቀበለ? ፍጡር ከሆነ፥ እንደ ጴጥሮስ ፍጡር ነኝና አትስገዱልኝ ለምን አላለም? ብለው የገዛ ራሳቸውን መጠየቅ አይገባቸውም ነበርን? ለፈታኙ ለዲያብሎስ የተናገረውን ቃል ረስቶት ነው ይላሉን? የሐዋ. 10፥25።

ወይስ የማይገባው መሆኑን እያወቀ፥ በራስ ወዳድነት ግድ የለም፥ ይስገዱልኝ፥ በማለት በውሸት ራሱን ማታለሉ ነው? ብለው የገዛ ራሳቸውን ለምን አይጠይቁም? ደግሞ ራሱን እንደዚህ አድርጎ የሚያታልል ከሆነስ፥ አርዮሳውያን ለምን ተስፋ ያደርጉታል? ምንም እንኳ በዚህ ምድር እንጂ፥ ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ባይኖራቸው ቅሉ፥ በአርማጌዶን ጦርነት መጥቶ የዓለምን ሀብትና ንብረት ቀምቶ ያወርሰናል» እያሉ የሚያደርጉት ጉጉትና ተስፋ የቱን ያህል ነው የሚያስተማምነው? ፊልጵ. 3፥18። ራሱን የሚያታልል ቀምቶ ይሰጠናል ተብሎ ተስፋ ይጣልበታልን? ዕብ. 6፥18። የለም. ነገሩ እንደዚህ አይደለም። አርዮሳውያን ትዕቢታቸውን አስወግደው የእምነት አቋማቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የተገለጸውን ትምህርት ቢያደምጡ የተገባ ነው። ዮሐ. 14፥6። 1ዮሐ. 5፥12፡20።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈትነው ለመጣ ዲያብሎስ «ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ እርሱን ብቻ አምልክ» ተብሎ ተጽፎአል ሲል የተናገረው እውነተኛ ነገር ነው። ይህ የተናገረው ቃል ከሚለወጥ የሰማይና የምድር ኅልፈት ይቀላል፡- ሉቃ.4፥7፡8። ማቴ. 24፥35።

ዳግም ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጀምሮ ሌሎች ሰዎች ሲሰግዱለትና ሲያመልኩት እያየ፥ ስግደታቸውንና አምልኮታቸውን ለምን ተቀበለ? ብለን የቅድሙን ጥያቄ እንደገና እንጠይቃለን።

መልሱ፡- በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር፥ በየውሃትና በትሕትና በሥጋ የተገለጸ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ሲሰግዱለትና ሲያመልኩት እያየ፥ ስግደታቸውን አምልኮታቸውን በሚገባ አጽድቆ የተቀበለላቸው፥ በአጭሩ የገዛ ራሱ ማንነቱን ወይም ማን መሆኑን ስለሚያውቅ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በሥጋና በመሢሕነት አቋም መጥቶ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፥ በዚህ ዓለም ቢገለጽም፥ ከዘላለም ጀምሮ ማን እንደሆነ የራሱን ህላዌ ያውቃል። ሚክ. 5፥2። ዮሐ. 17፥5።

1. እርሱ የምስጋና ጌታ ነው። 1ቆር. 2፥8።

   እርሱ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚኖር ዘለዓለማዊ ቃል ነው። ዮሐ. 1፥1። እርሱ ሥጋ የሆነ ቃል ነው። ዮሐ. 1፥14።

   እርሱ በሥጋ የተገለጸ አምላክና የመለኮቱም ምልዓት በሥጋው ያደረበት ነው 1 ጢሞ. 3፥16። ቈላ. 2፥9።

እግዚአብሔር አብ በወልድ ህልው ሆኖ እንደሚኖር ሁሉ፥ ወልድም በአብ ህልው ሆኖ ይኖራል፥ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ህልው ሆኖ ይኖራል። ዮሐ. 14፥11። 16፥14-15። 1ቆር. 2፥11፡12።

ስለዚህ ነው እግዚአብሔር አባቱ ለልጁ እንዲሰገድለት፥ ክብርና ምስጋና በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ያሉ ፍጥረታት ሁሉ እንዲያቀርቡለት ያደረገ።

## ወልድ እግዚአ ስብሐት /የምስጋና ጌታ/ ነው።

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር አባቱ ለልጁ እንዲሰገድለትና ክብር ምስጋናም /ስብሐት/ እንዲሰጠው አድርጎአል። ስለዚህም ሰዎችና መላእክት በየደረጃቸው ሰግደውለታል።

ይኸውም ከሰዎች ወገን ከሰብአ ሰገል ጀምር እስከ ለምጻሙ ሰው ከመላእክትም አራቱ እንስሳ፥ ሃያ አራቱ ጌቶች ሊቃነ መላእትና ቍጥር ስፍር የሌላቸው ኃይላት በጠቅላላው የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ክብር ምስጋና ኃይልም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ በሚያቀርቡበት ጊዜ አራቱ እንስሳ «አሜን» እያሉ፥ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም ሲሰግዱለት ታይተዋል። ራእ. 5፥5-14።

ስለዚህም ለቃለ እግዚአብሔር ወልድ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚህ ያለው ክብር፥ ምስጋና ስግደት ከተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ ሲሰጠው ያየ ሰው ይህ ለቃለ እግዚአብሔር ወልድ የተሰጠው ምስጋና ክብር ስግደት ምናልባት እንደ እንግዳ ነገር የሚሆንበትና የሚመስለው ይኖር ይሆን? ይህ ምስጋና ክብር ለእግዚአብሔር ቃል ወልድ ዘለዓለማዊ ገንዘቡ እንደነበረ ምናልባት አያውቅ ኖር ይሆን?

ወልደ እግዚአብሔር ምንም እንኳ ለተሳዳቢዎች ጠላቶቹ ደስ ባይላቸውም፥ ከዘለዓለም በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር፥ በየውሃትና በትሕትና የባርያን መልክ ወስዶ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ተዋርዶ ዓለሙን በማዳኑና በመቤዠቱ፥ ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ተሰጥቶታል። ፊልጵ. 2፥6-11።

ከፍጡራን የተሰጠው ስግደት ክብር አምልኮትና ምስጋና፥ እንደዚሁም እግዚአብሔር አባቱ ስለ ሞቱ ሕማም ያቀዳጀው የክብርና የምስጋና ዘውድ የሚገባው ነውና በሰማይ በምድር «አዎን አሜን» ተብሎለታል። ዕብ. 2፥9። 2ቆር. 1፥19፡20።

ይሁን እንጂ ምስጋናው በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም። የእግዚአብሔር ልጅ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም «የምስጋና ጌታ» መሆኑ ደግሞ መዘንጋት የለበትም።

እንዲያውም ከዚህ በላይ ከፍጡራን ሁሉና ከእግዚአብሔር ከአባቱ ሲሰጠው የታየው ምስጋና ክብር ከሥር ከመሠረቱ በዘለዓለማዊ ባሕርዩ «የክብርና የምስጋና ጌታ» ከመሆኑ የተነሣ ነው። 1ቆር. 2፥8።



የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ «የምስጋና ጌታ» ተብሎ የተነገረለት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፥ «የምስጋና ጌታ» መባል በመቀበል በስጦታ የተገኘ፥ የመገባ ስም ብቻ ሳይሆን፥ የባሕርያዊ ስም መሆኑ መታወቅ አለበት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ልዑል እግዚአብሔር «የምስጋና ወይም የክብር አምላክ፥ የምስጋና ወይም የክብር ንጉሥ፥ የምስጋና ወይም የክብር ባለቤት እየተባለ እንደተጠራ እናገኘለን። በግዕዙም «አምላከ ስብሐት፥ ንጉሠ ስብሐት፥ እግዚአ ስብሐት» ተብሎ ይነበባል። መዝ. 23/24/፥9። የሐዋ. 7፥2። 1ቆር. 2፥8።

በዚህ ጊዜ የምስጋና /የክብር/ አምላክ፥ የምስጋና ጌታ የምስጋና አምላክ፥ የምስጋና ንጉሥ» ተብሎ ሲነገር፥ ምን ትርጉም ይሰጠናል? ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምን ባለ ትምህርት ተገልጾአል? ብለን የጠየቅን እንደሆነ፥ በተመርሆ ልቡናዊ አገላለጽ መመልከት ይኖርብናል።

«የምስጋና አምላክ ወይም የምስጋና ንጉሥ ወይም የምስጋና ጌታ ተብሎ ሲነገርለት፥ ምስጋና የአምላክነቱ ባሕርያዊ ግብር የሆነለት፥ ምስጋና የንጉሥነቱ ባሕርያዊ ገንዘብ የሆነለት፥ የምስጋና ጌታ፥ የምስጋና ባለቤት ማለት ሆኖ እናገኘዋለን። ኢሠ. 9፥5። ዕብ. 13፥21።

ይህም ከፍጡራን ሲሰጠውና ሲቀርብለት በሚታይ ብቻ ሳይሆን፥ ፍጥረታት ሳይፈጠሩ በፊትም /ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ/ ምስጋናው ክብሩ የባሕርዩ ገንዘብ የዘለዓለማዊ መንግሥቱ ባሕርያዊ ይዞታ የመለኮታዊ ጌትነቱ መታወቂያ ሆኖ ነው የሚነገር። መዝ. 102/103/፥19-22። 144 /145/፥2፡13።

እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የምስጋና ጌታ» ሲባል፥ እንደዚሁ እንደ አባቱ መሆኑን በሚገልጽ አነጋገር ተነግሮለታል። ይኸውም «ቢያውቁስ ኖሮ /የምስጋናን ጌታ የክብርን ጌታ/ ባልሰቀሉም ነበር» ተብሎ ተነግሮለታል። 1ቆር. 2፥8።

እንደ አባቱ መሆኑን በሚያስገነዝብ ገለጻ ተነገረለት ስንል፥ አንባቢው በጥቅሱ ያለውን የልቡናዊ ተመርሆን ይረዷል።

ከዚህም በላይ ጌታችን ራሱ «አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አክብረኝ» ያለውን ምስክርነት ይገነዘቧል። ዮሐ. 17፥5።

በዚህ ጊዜ ዓለማት ሳይፈጠሩ ለወልድ በአባቱ ዘንድ የነበረው ምስጋና በሚለው ቃል ላይ፥ አንባቢው ቆም ብሎ በእነዚህ ዝርዝሮች እንዲያስብበት እንጠይቀዋለን።

ይኸውም፡-

1. ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ለወልድ የነበረው ክብር፥ ምስጋና፥ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የእርሱ ሆኖ እንደኖረ፥

2. ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ይህ ለእርሱ የነበረው ክብር ምስጋና፣ ከአባቱ ዘንድ የእርሱ ሆኖ እንደኖረ፤

3. ይህ በአባቱ ዘንድ የነበረው ክብር ምስጋና ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም የእርሱ የራሱ ሆኖ እንደነበረ ማስገንዘብ ነው።

ስለዚህ «የክብር ጌታ የምስጋና ጌታ /እግዚአ ስብሐት/ ሲባል፣ ምስጋናው /ክብሩ/ ምንም ባልነበረ ጊዜ /ፍጡራን ባልነበሩበት ጊዜ/ የእርሱ የራሱ የባሕርዩ እንደነበረ ያስገነዝባል።

እንግዲህ ዓለም ሳይፈጠር ከአባቱ ዘንድ የነበረው ይህ ክብር የባሕርዩ ክብር እንደመሆኑ መጠን፣ የማይሻርና የማይለወጥ ነው።

በሥጋ በተገለጸ ጊዜም «እርሱ ከሁሉ በላይና የተባረከ አምላክ ነው። ሮሜ 9፥5።

«ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» በተባለ ጊዜም፣ አንድያና የተወደደ ልጅ ሆኖ በአባቱ ክብር መጠን እንዳለው የሆነውን ክብሩን አሳይቶበታል። ዮሐ. 1፥14። 2፥11።

ጌታችን የዓለም ቤዛ ሆኖ በተሰቀለና በሞተ ጊዜም «የክብር የምስጋና ጌታ እንደሆነ አስታውቆበታል። ሥቃዮቹ አይሁድ እንደዚህ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ «የምስጋናን ጌታ በሰቀሉ ነበርን?» ተብሎለታል።

ይህ የአይሁድ አድራጎት ለአርዮሳውያን መልእክት ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ። በአይሁድ የደረሰው በአርዮሳውያን ላይም እንዳይደርስባቸው እጅጉን ያስፈራልና። የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምስጋና ጌታ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ፣ በአሁኑ ጊዜ እየሰደቡት ለመኖር ባልቃጡም ነበርና ነው። 1ቆሮ. 2፥8። 16፥22።

በትንሣኤውም እርሱ የክብር የምስጋና ጌታ እንደሆነ ነው። ትንሣኤ በአብ ክብር ነውና። ሮሜ 6፥14። የሐዋ. 3፥23።

በዕርገቱና በአባቱ የምስጋና ዙፋን በመቀመጡ የክብር ዙፋን ከዘለዓለም መኖሩን አስገንዝቦበታል፡- ዕብ. 1፥3-10። ፊልጵ. 2፥6-11። ራእ. 5፥5-13።

ዳግመኛ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜም በዚሁ በአባቱ ክብርና ምስጋና ይገለጽበታል። ማቴ. 25፥31።

ስለዚህ «የክብር የምስጋና ጌታ» ሲባል፣ ይህን ምስጋናና ክብር በመቀበል ብቻ ያገኘው ሳይሆን፣ ከመሠረቱ ዓለም ሳይፈጠር፣ ከአባቱና ከቅዱስ መንፈሱ ዘንድ የነበረ ዘለዓለማዊ ክብር፣ ምስጋናም ነው።

በሥጋ ተገልጾ በትሕትና በየውሃት የሚከናወን ለሰው ልጆች ማዳኛ የሚሆነውን ሥራ በፈጸመ ጊዜ፣ ከሰዎች ከመላእክትም ክብር ምስጋና ስግደት ቢቀርብለት፣ ከአባቱም የክብር የምስጋና ዘውድ ቢቀዳጅ፣ ከቅዱስ መንፈሱም



ቢከብርና ቢመሰገን፣ ከመሠረቱ በባሕርዩ «የክብር የምስጋና ጌታ» በመሆኑ እንጂ፣ በከንቱ የተሰጠው አይደለም። ለእርሱም እንግዳ ነገር አይደለም። ፊልጵ. 2፥6-11። ዕብ. 2፥9። ዮሐ. 16፥14። 8፥39። ይህ የተቀዳጀው ክብርና ምስጋና ከቤቱ ውጭ የሄደ አይደለም። በመሢሐዊ ልጁ እጅ እንዳለ ነው ያለው።

አባቱ «ክብሬን ለሌላ አልሰጥም፤ ምስጋናዬንም ለጣዖታት አልሰጥም» ብሎ የለምን? ይህ አባባል የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን፣ አይታበልምና አይፈርስም ። ኢሳ. 42፥8።

አሁንም ክብሩን ምስጋናውን ለሌላ አልሰጠም። በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ቃል ግን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአባቱ ዘንድ በነበረው ምስጋና ነው የተመሰገነ። ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ያው «የክብር፣ የምስጋና ጌታ» ነውና። ሃሌ ሉያ ። ዮሐ. 17፥5። 1ቆሮ. 2፥8።

## ዱሮም ነቢዩ ኢሳይያስ የወልድን ክብር አይቶ ነበር።

ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንትም «የክብርና የምስጋና ጌታ» መሆኑን ለነቢዩ ለኢሳይያስ ተገልጾለት ነበር።

ነቢዩ ኢሳይያስ ንጉሡን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፣ ... ሱራፌልም በልሳነ እሳት «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ምድር ሁሉ ከክብሩ ሞልታለች» እያሉ ሲያመሰግኑት አይቶ ነበር። ኢሳ. 6፥1-13።

እነሆም ንጉሡ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፣ በዚህ በሚያስፈራ ግርማና ክብር ሲገለጽ፣ የክብሩ ብርሃን የአካሉ ምሳሌ በሆነ በክብርና በምስጋና ጌታ በልጁ ነበረ የተገለጸው። ዕብ. 1፥1-3።

ይህ ለነቢዩ በራእይ የተገለጸለት ምድርን በክብሩ የሞላት የእግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ መልክዓዊ ግርማ፣ ለማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌና የክብሩ ብርሃን የሆነ የክብር የምስጋና ጌታ ወልደ እግዚአብሔር ነበረ። ቈላ. 1፥15፤16። ዕብ. 1፥3። 1ቆሮ. 2፥8።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነቢዩ ኢሳይያስ ራእዩን ሲያይ የተናገረውን ቃል በቃል ጠቅሶ «ኢሳይያስ ክብሩን ስለአየ ይህን አለ፣ ስለ እርሱም ይህን ተናገረ» ብሎ ነቢዩ ያየው እግዚአብሔራዊ ክብር ወልድ እንደነበረ ገልጾ ማስረዳቱን ማስተዋል ነው። ዮሐ. 12፥40፡41።

ቃለ እግዚአብሔር ወልድም የማይታየው እግዚአብሔር ምሳሌና የክብሩ ብርሃን /ነጸብራቅ/ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልጽ ነውና፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲያብራራው «ነቢዩ ኢሳይያስ ክብሩን ባየ ጊዜ፣ ይህን አለ፣ ስለእርሱም

ይህን ተናገረ!» በማለቱ፥ በሥጋ የተገለጸው ወልድ ማን እንደሆነና ጥንትም እንዴት እንደነበረ አሳየ።

በዚሁ ራእይ ኢሳይያስ ያየው የእግዚአብሔር ክብር፥ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን፥ ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲያረጋግጥ፥ ነቢዩ ኢሳይያስ በዚሁ ትርኢት የሰማው የእግዚአብሔር ድምፅ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ አብራርቶ አስረድቶአል። የሐዋ. 28፥25-27።

ይህን ከተገነዘብን ዘንድ በአጠቃላይ የምናየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከመገለጹ አስቀድሞ ቢሆን፥ በዘለዓለማዊ የአምላክነት ባሕርዩ «የክብር ጌታ የምስጋና ጌታ፥ የተባረከ አምላክ እንደመሆኑ መጠን፥ በሱራፌል ዘንድ «ቅዱስ፥ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ» እየተባለ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፥ ሲቀደስ፥ ሲሠለስ ሲመሰገን፥ ሲወደስ የኖረ መሆኑን ነው።

አሁንም በእኛና በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ፦ ብቻውን አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ፥ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ፥ ክብር፥ ምስጋና ስግደት አምልኮት ይሁንለት! ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም። አሜን።